የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የተሰጠ ልዩ የኃዘን መግለጫ

**ኅብረቱ አንድ ምሰሦውን አጣ!**

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በአቶ ሙሉጌታ ኃይሉ ድንገተኛ ሞት የተሰማውን ጥልቅ ኃዘን የሚገልፀው በሕይዎት ዘመናቸው ያደረጉትን አኩሪ አስተዋፅዖ በአንክሮ በመዘከር ነው፡፡**

**አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ ለሚወዷት አገራቸው ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ለሕዝቧም እኩልነትንና ፍትኅን ለሚያጎናፅፍ የሥርዓት ለውጥ ከአርባ ዓመታት በላይ ወለም-ዘለም ሣይሉ የታገሉ መንፈሰ-ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ነበሩ፡፡ አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ በተፈጥሮኣቸው ረጋ ያሉ፣ እጅግ ታጋሽ፣ ቁጥብ፣ የሰውን አሣብ የማዳመጥና የመግባባት ልዩ ባኅሪን የተላበሱ በመሆናቸው ለሥርዓት ለውጥ በቆሙ ድርጅቶች መኻል መቀራረብ እንዲፈጠርና የጋራ የትግል መድረክ እንዲቋቋም በተደረጉ ያልተቋረጡ ጥረቶች ሁሉ በጣም የጎላና ግንባር ቀደም ሚና የተጫዎቱ ጨዋ ኢትዮጵያዊ ነበሩ፡፡ በዚኽም ድርጅታቸውን መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊት ንቅናቄን (መኢሶንን) በመወከል ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ጀምሮ እስከ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ድረስ ከምሥረታ አንስቶ በልዩ-ልዩ የኃላፊነት እርከኖች ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሣይሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡ በልዩ-ልዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችም ተሣትፈዋል፡፡**

**አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ በውጭ አገር፣ በተለይም በዋሽንግተን ዲሲና በአካባቢው በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ለሥርዓት ለውጥ የቆመው ክፍል ቋሚ አርማ ተደርገው የሚታዩ ታጋይ ነበሩ፡፡ እኚኽ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ትግል ከጀመሩበት የወጣትነት ዕድሜአቸው ጀምሮ እስከ ዕለተ-ረፍታቸው ድረስ በአገራቸው ፍትኃዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና ዜጎች መብቶቻቸው እንዲከበሩ የሚደረገው ትግል ግቡን እንዲመታ በተቃዋሚው ጎራ መኻል በመቻቻልና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ መከተልን አስፈላጊነት በፅንሰ-አሣብ ብቻ ሣይሆን በተግባር መተርጎም ያለበት መሆኑን ያመኑና የሱም መገለጫ የነበሩ ታጋይ ነበሩ፡፡
አቶ ሙሉጌታ ብልሹ ሥርዓት እንጂ ኢትዮጵያዊ ጠላት አልነበራቸውም፡፡ በመሆኑም በአገርና በሕዝብ ጉዳይ፣ አልፎም አጠቃላይ በሰው ልጆች ክብርና ደኅንነት ላይ ከማንም ጋር መወያየት፣ በጥሞና መደማመጥና አሣብ መቀያየር፣ እምነታቸውንም በረጋ ሁኔታ ማስረዳት ባኅሪያቸው ነበር፡፡**

**አቶ ሙሉጌታ ከመደበኛ ድርጅታዊ አስተዋፅዖ በተጨማሪ ለልዩ-ልዩ ድርጅታዊ ስብሰባዎች ለሚመጡ፣ አልፎም በትግሉ ሣቢያ ለሚያውቋቸውና ለግል ጉዳያቸው ወደ ዋሽንግተን ብቅ ለሚሉ ኢትዮጵያውያን ሣይቀር ቤታቸውን የአብርሃም ቤት አድርገው ባስፈለጋቸው ጊዜ ሁሉ ቁልፍ ይዘው እንደራሣቸው ቤት አይተው እንዲጠቀሙ ከማድረግ ጀምሮ ያስተናገዱ፣ ወገናዊና ወንድማዊ ትብብራቸውን በደስታ የለገሱ በጣም ቸርና ትኁት ሰው ነበሩ፡፡**

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በተለይ፣ ለለውጥ የቆመው ተቃዋሚ ጎራ በአጠቃላይ የአቶ ሙሉጌታ ኃይሉ በድንገተኛ ሞት ከዚኽ ዓለም መለየት የሚፈጥረው ክፍተት ቀላል እንዳልሆነ ይገነዘባሉ፡፡ በዕድሜ-ልክ ታጋይ ሙሉጌታ ኃይሉ ድንገተኛ ሞት ኅብረቱ በእርግጥም አንዱን ምሰሦውን አጥቷል፡፡**

**ለአቶ ሙሉጌታ ዘላለማዊ እረፍትን፣ ለሥጋና ለትግል ቤተሰባቸው ሁሉ መጽናናትን ስንመኝ፤ ለሚወዷት አገራቸው ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ልዕልናና ክብር ዕድሜ-ልካቸውን ላደረጉት ትግልና አስተዋፅዖ ሁሉ ያለንን ከፍተኛ አክብሮት በኩራት በመግለፅ ነው፡፡**

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ዋሽንግተን ዲሲ፤ ግንቦት ፪ ቀን ፪ ሺህ ፬ ዓ/ም (May 10, 2012)**

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73796
WashingtC 20056-3796, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel. 202 361 7162

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ  The Hague, Netherlands
ስልክ Tel/Fax 31 70 394 6132